

# ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች

ከማተቤ መለሰ ተሰማ

## መግቢያ

በመጀመሪያ ደረጃ ይህነን ቃል ለዚህ ጽሁፍ አርእስት እንዲሆን ስመርጠው የገጸ ባህሪያትን አሣሣል የታሪክን አወቃቅር የዘከረ የጸሃፊነት ሙያውን በመካን የአዋቂነቱን በትረ ሥልጣን ጨብጫለሁና ህሌናየ ያረገዘውን በሙሉ በተባ የብ እር ቱርፋት ወልጀ ወደምፈልገው አቅጣጫ በማትመም የአንባብያንን መንፈስ የመማረክ ክህሎቱ አለኝ ብየ በማሰብ ስለመጽሀፍ ቅዱስና ስለኢትዮጵያ ታሪክ መነሻ ቀምሮ መንገድ ተልሞ መድረሻ ወስኖ በዋቢ አስደግፎ በአማረ ቃል የተከሸነ ጽሁፍ ለማቅርብ አልሜ እንዳልሆነ አንባብያን እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ ምክናያቱም የታሪክንና የመጽሀፍ ቅዱስ ምሁራንን ስራ ባልተሟላ ሙያ እንደመሻማት ስለምቆጥረው ሥራን ለባለሙያው መተውን በመምረጥ፣

በዚያ ፋንታ ግን ዛሬ በስሜቴ አጭሮ የህሌና እና የመንፈስ ጉልበቶቸን አስተባብሮ ብእርና ወረቀት እንዳገናኝ ያዘዘኝ ህዝብንም እግዚአብሔርንም ታሪክንም የናቀው ከውልደቱ እስከ ዕለተሞቱ ውሸትንና ክህደትን ልብሱና ጉርሱ ያደረገው ነፍሰ ገዳዩ፣አረመኔው፣ኋላቀሩና ዘርኛው፣በቀለኛው በአንድ ቃል የሀገር እግዚያብሐር ኢትዮጵያ መጥፊያ የተፈጠረው  የወያኔ ቡድን በሚሰጠን የቤት

ስራ እንደሰናወር ግንበኞች በሃሳብ እየተለያየን በአመለካከት እየተራራቅን እርስ በርስ ስንቧጨቅ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሊጠፉ ከመጨረሻው እርከን ላይ ቆመው እየተማጸኑ እንደሆነ ስለሚሰማኝ ውስጤን ይገልጽልኝ ይሆናል ከሚል የጭንቀት ሃሣብ በመነሣት ነው ፣በሌላ በኩልም ሰው በሰውነቱ ወደዚህ ዓለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ሊያከናውናቸው የሚገባው ተፈጥሮአዊ፣ሰባአዊና ሞራላዊ ግዴታወች አሉበት ብዬ በጽናት አምናለሁ እንደ እኔ አመለካከት የሰው ልጅ በዚች ዓለም የአጭር ጊዜ ቆይታውን የሚያሣልፉት ያለምንም ሃይባይና ተቆጣጣሪ ለብቻው አይደለም ብየ አስባልሁ ይልቁንም ስፊ ህዝብን ያህል ሃያል አዛዥ ታሪክን ያህል ሃቀኛ ተሟጋችን በጀርባው ያስለፈ ሃላፊነት ተሸክሞ እንጅ፣ ቁም ነግሩ ግን ስንቶቻችን ነን ሰባዊ ግዴታችንን ለሃገር በሚጠቅም ለወገን በሚበጅ መልኩ እየተወጣን ያለነው የሚለው ሲሆን በበኩሌ ጠቅለል አድርጌ ስመለከተው ዛሬ ኢትዮጵያውያን በ3 ትላልቅ ጎራ የተከፈልን ይመስለኛል፣

**1ኛው** ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር ከዓለም ካርታ ተፍቃ እንድትጠፋና ኢትዮጵያዊ ነኝ በማለት አፍ ሞልቶ ደረት ነፍቶ የሚናገር ዜጋ እንዳይኖር ሌት እንቅልፍ ቀን እረፍት አጥቶ በመስራት ላይ ያለው ካሃዲው የወያኔ ቡድንና እንባ ጠባቂዎቹ ሲሆን

**2ኛው** የሃገሩ መጥፋት የወገኑ ሞት፣ እራብ ፣እርዛት. ስደት፣ ውርደት ወ.ዘ.ተ እያሣረረው፣ እያንገበገበው የቻለ ቆሞ ሲሞቱ ከመኖር ሞትን በሞት ሽሮ ማለፍ ሀያውነት ነው በማለት ፊትለፊት ገጥሞ የሚዋጋውና ያልቻለው ደግሞ ይህንን ነፍስገዳይ ቡድን ለአንዴና ለመጨርሻ ጊዜ ለመንቀል በተለያዩ የትግል ስልቶች ተሰልፎ እየታስሰረ እየተፈታ የጊዜ፣ የገንዘብ ፣የአእምሮና የጉልበት መሷእትነት በመክፍልና አስፈላጊ ሆኖ ጊዜና ቦታ ከፈቀደም መራራውን ጽዋ ለመጎንጨት በቁርጠኝነት የተሰለፈው ሃይል ነው፣

**3ኛው** የወገኑ ማለቅ ሳይኮነስርው የሀገሩ መጥፋት ሣያሳሥበው የእራሱን ኑሮ ብቻ በማደላደል ቢቀዘቅዝ በእጀ ቢፋጅ በማንኪያየ እንደሚባለው ሁሉ ዛሬም በወያኔ አይን ሣልገባ ተከብሬ እኖራለሁ አጋጣሚ ሆኖ ወያኔ ከተሸነፈም ምላሴን አሳምሬ ለሀገሬ ስቆረቆር የኖርሁ በመምሰል እቀርባለሁ ብሎ በማሰብ ካሃዲውና አርበኛው ከሚለያዩበት መንገድ ላይ ቆሞ ለሁለቱም ዲንጋይ በማቀበል ላይ የሚገኘው መሀል ሰፋሪው ቡድን ነው፣ እንግዴህ ልዩእነቱ በማልማትና በማጥፋት በታማኝነትና በካሃዲነት ብሎም በመሃል ሰፋሪነት ተከፋፍለን እንሰለፍ እንጅ ከላይ እንዳልኩት የተፈጥሮ ግዴታችን የሚያዘንን እየከውን፣

ይመስለኛል በበኩሌ ነገ ላይ ስንድርስ ማን ምን እንደሆነና ማን ምን እንዳከናወነ የሚያበጥርው አንድ አቢይ ቁም ነገር እንዳለ ግን ከምር አምናለሁ፣ እሱም ተግባር ነው ተግባር በህዝብና በህግ ፊት ፍርድ የሚስጥበት የታርክ ሚዛን ነውና፣ አሁን የእኔ ችግር ያለው ለጥፋት ከተሰለፍውና መሀል ከሰፈረው ላይ አይደለም፣ ለሀገሬ የሚበጀውንና በሰውነቴ የማምንበትን ሰርቸ ውጤቱን ዘር፣ ሃይማኖት ሣልለይ ለኢትዩጵያ ህዝብ ለማስረከብ ስጋየን በእምነቴ እረትቻለሁ በማለት ለመሷዕትነት የተሰለፈው ሃይል ሆደ ባሻ መሆን፣ መቻቻል ማጣት፣ እኔ ያልመራሁት ትግል ድራሹ ይጥፋ አይነት አቋም ማራመድ ወ.ዘ.ተ. እንጅ ለሰሚው ግራ የሆነውና እልባት የጠፋለትም አሳዛኝ ድራማና ወደፊትም ካልታሰበበት እኛ እንደ ዳይኖሰር እርስ በርስ ስንባላ ሃገራችን መጥፋቷ ሳይታለም የተፈታ ነው፣

## እውን ታሪክ እራሱን ይደግማል?

የኢትዩጵያን ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት ከ 1762 እስከ 1845 በነበረው ወቅት ልክ እንደዛሬው ህዝቦቿ ተከፋፍለው ማእከላዊ መንግስት ጠፍቶ ልማት ስልጣኔዋና እድገቷ ወደኋላ ተገፍቶ ለሁለንተናዊ ውድቀት የተጋለጠችበት አጋጣሚ ነበር፣ የሚገርመው ነገር ደግሞ ከዚያ በፊት በሰላም የስልጣን ሽግግር እያደረጉ በሺዋች ለሚቆጠሩ አመታት ኢትዩጵያን ብቻ ሣይሆን ብዙ የዛሬ አጎራባች ሀገሮችንም ጭምር ሲያስተዳድሩ ከኖሩት ነገሥታቶቻችን መካከል አጼ እዩያስን የልጅ ባላቸው የሆኑት የትግራዩ ተወላጅ እራስ ስሑለ ሚካዔል የንጉሱን የቤት አሽከሮች በጥቅም አባብለው አሣንቅው በማስገደላቸው ነበር ለ70 አመታት ያሁሉ ጥፋት የደርሰው፣ ዛሬም ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዲሉ ሆነና ትግራይ የበቀሉት ጉዶች ናቸው ኢትዩጵያን በማፍረሱ ሥራ ላይ ተጠምደው ያሉት፣ የእናት ሆድ ዥጉርጉር ነው እንደሚባለው ሁሉ እራስ ስሑለ ሚካዔል ያፈረሷትን ኢትዩጵያን ትግራይ የበቀሉት አጼ ዩሐንስ ፣ቲዎድሮስ በጣሉት መሰረት ላይ የአንድነት ግድግዳውን ተክለው የጣሪያውን ሥራ ለምኒልክ እንደአስተላለፉ ሁሉ ዛሬም እነመለስ ዜናዊ እያፈረሷት ያለችዋን ሀገር መልሶ የሚገነባ ሌላ ዮሐንስ ከትግራይ እንደሚፈጠር ተስፋ አለኝ ፣ታሪክ በክፉው ብቻ ሣይሆን በበጎውም እራሱን መድገም ስለአለበት፣

## የእስራዔሉ አቢሜልክና አቶ መለስ ሲነጻጸሩ፣

አንድ ህዝብ የሚገባውን መሪ ከእግዚአብሔር ያገኛል ይባላል ፤በእውነት ይህ ትውልድ ምን በደል ፈጽሞ ይሆን በጭካኔ የተሞሉ በህዝብ እርሀብ፣ እርዛት፣ ሞት ሰቆቃና ዋይታ ሀሴት የሚያደርጉ ባለስልጣናትን የላከበት እዚህ ላይ ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ከሰፈረው ከአቢሜልክ ጋር የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ስለሚመሳሰል ማንሣት እፈልጋለሁና መጽሐፉ እንዲህ ይላል፣ የእስራዔል ህዝቦች በእግዚያብሔር ፊት በደል ሰሩ፣ እግዚያብሔርም ለምድያማውያን አሣልፎ ሰጣቸውና ለ7 አመት በአሰቃቂ ሁኔታ ገዟቸው ይላል፣ አዋ! ውድ አንባብያን እነሱ ለ7 አመት እኛ ግን 18 አመት ሆኖንም ገና ፍዳችን አላከተመም፣ እግዚአብሔር አንድን ሕዝብ ሲቀጣው ሲያስብ መሪውን ያከፋበታል ይባል የለ ፣ እኛም ፈጣሪያችንን ስለአስቀየምነው ይመሥለኛል እስራዔላውያንን ለምድያማውያን አሣልፎ እንደሰጠ ሁሉ ኢትዩጵያውያንንም ምንም እንኳን የእራሱ ወገኖች ቢሆኑም ለጨካኞች አሳልፎ የሰጠው ፣ ታሪኩ ሲቀጥል ከዚህ መአት ያድናቸው ዘንድ እስራዔላውያን ወደ አምላካቸው ጸለዩ እኛስ ስንቶቻችን እንሆን የደረሰብንን በደል ለእግዚአብሔር የምንነግረው፣ እግዚአብሄርም ሰማቸውና ከመካከላቸው ጌዲዩንን አስነሣላቸው፣ ለእኛም እግዚአብሔር ኢትዩጵያዊ ጌዲዩን ያስነሣልን እና ጌዲዩን እስራዔላውያንን ከምድያማውያን ነጻ ካወጣቸው በኋላ ለ40 አመት በሰላም በመኖር ከተለያዩ ሴቶች 70 ወንድ ልጆችን ወልዶ ሞተ፣ ከ70ዋቹ ልጆቹ መካከል ከአንዷት ሴኬማዊት ሴት የተወለደው አቢሜልክ ከወንድሞቹ ተለይቶ ወደ እናቱ ሀገር በመሄድ የሴኬምን ህዝብ ስብስቦ በ70ወቹ የጌዲዩን ልጆች ከምትገዙ እኔ ወንድማችሁ ባስትዳድራችሁ ይሻላልና እርዱኝ ሲላቸው እሽ ብለው 70 ጥሬ ብር በማዋጣት ሰጡትና በዚያ ብር የማይረቡ ቦዘኔዎችን በመግዛት ወደ አባቱ ቤት ሄዶ አንዱ ተደብቆ ሲያመልጥ ሌሎች ወንድሞቹን በጠቅላላ ደመሰሣቸው ይለናል መጽሃፍ ቅዱስ፣ ወደ እኛ ስንመለስ ደግሞ አቢሜልክ ወንድሞቹን ለመደምሰሥ የሴኬምን ቦዘኔዎች እንዳሰለፈ ሁሉ አቶ መለስ ዜናዊም ኢትዩጵያንና ኢትዩጵያዊነትን ለማጥፋት በመጀመሪያ ሌላው የኢትዩጵያ ህዝብ የትግራይን ህዝብ የበደለ በማስመሰል የትግራይን ወጣቶች አሳምነው ደደቢት አስገቧቸው፣ ስልጣን ሲይዙ ደግሞ እነሱንም በማግለል ምርኮኛውንም ዱርየውንም ከየትም ለቃቅመው በማሰለፋቸው በአሁኑ ወቅት ህዝብን በጥይት

ብቻ ሣይሆን በእርሀብ በእርዛት በበሽታ የሚረሸኑት ፍርድን የሚገመድሉት የጥፋት መልከተኞች በሙሉ በኢትዮጵያዊነታቸው የማያምኑ ህዝቡንም የማያውቁትና ህዝቡም የማያውቃቸው በአንድ ወይንም በሌላ መልኩ ሞራላዊ ስብናቸው የወደቀ በ70 ጥሬ ብር እንደተገዙት እንደ ሴኬም ቦዘኔዎች ያሉት ናቸው፣ ውድ አንባብያን ወደ መጽሐፍ ቅዱሱ ልግባ ቀጥሎ እንዲህ ይለናል፣ አቢሜልክ ወንድሞቹን ደምሥሥ ሲመለስ ተደብቆ ከሞት የተረፈው ወንድሙ ኢዩአታም በእርቀት ሆኖ እናንት የሴኬም ሰዋች አዳምጡኝ በማለት ጆሮአቸውን እንደቸሩት ሲረዳ ፣ ከእለታት አንድ ቀን ዛፎች ተሰብስበው ንጉስ ለመሾም ወሰኑና እንዲነግሱላቸው መጀመሪያ ወይራን ፣ቀጥለው ወይንን ፣ቀጥለው በለስን ቢጠይቋቸው ንጉስ ከሆንን ለሰው ልጅ የምንሰጠውን አገልግሎት ማቆም ስለአለብን አይቻልም በማለት ተመሣሣይ መልስ ይሰጧቸዋል፣ በመጨረሻ ወደ እሾሃማዋ ቁጥቋጦ በመሄድ እንዲነግስ ቢጠይቁት ፈጥኖ እሺ በማለት አሁኑኑ የዛፍ ዘር በሙሉ ተሰብስቦ በስሬ ካልተጠለለ የሊባኖስ ዝግባ ሣይቀር በእሣት አጋየዋለሁ አላቸውና እናንተም ወንድሞቼን ፈጅታችሁ አቢሜልክን ስታነግሱ እውነት ነውን? እንግዴህ ከአቢሜልክ እሣት ወጥቶ የሴኬምን ህዝብ ይብላው፣ ከሴኬም ህዝብም እሣት ወጥቶ አቢሜልክን ይብላው፣ በማለት ተራግሞ ሸሼ ይለናል ፣ በኢዩአታም አንደበት እየተናገር የነበረው እግዚያብሔር ነበርና ያለው ሲፈጽም እናያለን፣ ወያኔ ኢትዮጵያን ሲወር ስንት ኢዩአታሞች ነበሩ የቡድኑን አጥፊነት አስመልክተው ትንቢት የተናገሩት፣ የጮሁት፣ ከኢትዩጵያውዩ ማንዴላ ከሚቹ የነጻነት ታጋይና ብሔራዊ አርበኛ ከክቡር ፐ/ር አስራት ወልደየስ ጀምሮ አያሌ ኢትዩጵያዊ ኢዩአታሞች የዚህን ዘረኛ ቡድን መርዝነት አስገንዝበውናል፣ በወቅቱ ሰሚ ጠፋና ዛሬ ሃገሪቷ ተቆራርጣ ማለቅ ብቻ ሣይሆን ኢትዩጵያና ኢትዩጵያዊነት ጨርሰው ለመጥፋት ከተቃረቡበት ደርጃ ላይ ደርሰናል፣ ይህንን ሁሉ ያመጣውና የወያኔን እድሜ ከሚገባው በላይ ያራዘመው የእውነተኛ ኢትዩጵያውያን አለመደማመጥና አለመስማማት ነው፣ በጋራ መታገል ባይቻል እንኳን የተቃዋሚ ተቃዋሚ ሆነን መሰለፋችንን ብናቆም በወገን ላይ ውርጅብኝ በማፍሰሥ የምናሣልፈውን ጊዜ ወደ ጋራ ጠላታችን ማዞር በተቻለ ነበር፣ ያ በአለመደረጉ በሁሉም ዘርፍ ድውይ የሆነው ወያኔ ዛፎች ሁሉ መጥተው በስሬ ካልተጠለሉ በእሣት አጋያቸዋለሁ እንዳለችው ቁጥቋጦ ሰጥ ለጥ ብላችሁ የግፍ አዝመራዩ መውቂያ ካልሆናችሁ በምድር ላይ አትኖሩም ባላለን ነበር፣

ከመጽሐፍ ቅዱሱ ኢዩአታም አባባል እንደተረዳነው ዛፎች ንጉሥ ፍለጋ ከላይታች እንደአሉ ሁሉ ከውጭም ከውስጥም በደረሰበት ከፍተኛ ጫና

ምክንያት የደርግ መንግስት ለመውደቅ ሲንገዳገድ ምዕራባውያን ይህች በአፍሪካ ቀንድ እስትራቴጅክ ቦታ ላይ ያለች ሀገር ከእጃቸው ሣትወጣ እነሱ በሚጎልቱት አሻንጉሊት መንግስት ለስሙ በተዛዋሪ እንደዛሬው በእራሣቸው እንድትመራ ለማድርግ በነበራቸው እቅድ መሰረት ለጥቅሜ ይሰራል ብለው የገመቱትን ሁሉ ግለስብም ይሁን ድርጅት ጠይቀዋል፤ ግን ሃሣቡ ከቀረበላቸው ብዙዎቹ እነዚያ ዛፎች ሲጠየቁ መንገሱንስ እንንገስ በኋላ ግን ለሰው ልጅ የምንስጠው አገልግሎት ይቋረጣል በማለት እንደመለሱ ሁሉ ጥያቄው የቀረበላቸው እውነተኛ ኢትዩጵያውያን ሥልጣኑን እንረከብ ግን የኢትዩጵያንና ኢትዩጵያውያንን ጥቅም እናንተ በምትፈልጉት መልኩ አሣልፈን አንሰጥም ሲሉ ቁርጥ አቋማቸውን ሣያመነቱ በማሣወቃቸው ምዕራባውያኑ ፍለጋቸውን ሲቀጥሉ እንደ ቁጥጦው አናሣውና የኢትዩጵያዊነት ጠላት ከሆነው ከወያኔው ቡድን በመደረሱና እነ አቶ መለስም የተባሉትን ሁሉ እንደሚፈጽሙ ቃል በመግባታቸው ከመንገሣቸው ከ2አመት በፊት ነበር አልጋ ወራሺነቱ የተሰጣቸው፤

ውድ አንባብያን የአቢሜልክ ታሪክ ስለአላለቀ ወደ መጽሐፍ ቅዱሣችን እንመለስ ፣ ይህ ሰው ለ3አመት በእስራዔል ላይ ከነገሰ በኋላ ኢዩአታም እንደተራገመው እግዚአብሔር አቢሜልክንና የሴኬም ሰዎችን እሣትና ጭድ አደረጋቸው ፤አዎ! የእኛን ጉዶችም የሚጠብቃቸው ይኸው ነው፤ በስሙ በመነገድ እነሱ ለበሉ የትግራይን ህዝብ ከሌላው የኢትዩጵያ ህዝብ ጋር አቃቅረውት አይቀሩም፤ እናም አቢሜልክ ወንድሞቹን ስለገደለ የሴኬም ሰዋች ደግሞ ስለተባበሩት ብድራቸውን ይከፍሉ ዘንድ እርስ በእርስ ተዋጉና በፊት አቢሜልክ ጨፈጨፋቸው ሸሺተው ዋሻ ውስጥ ቢገቡ የዋሻውን በር በእንጨት ክምር አዘግቶ በእሣት አቃጠላቸው፤ አቢሜልክንም አንዲት ሴኬማዊት ሴት በወፍጮ ድንጋይ እራሱን መትታ ገደለችው ይለናል መጽሕፍ ቅዱስ፤ የውሻ ደም የማያስቀርው መዳህኒት ዓለም በአምሣሉ የፈጠረውን የስውን ልጅ ደም እንደጅረት ውሀ ያፈሰሰውን፤ ህዝብን በእርሃብ፤ በእርዛት ፣ እየቀጣና እየተበቀለ ያለውን የወያኔን ቡድን እንዴትና በማን ብድራቱን ይከፍለው ይሆን ፣ ጊዜ ለሁሉም ቁልፍ መፍቻ ስለሆነ እሱ መልስ ይስጥበት፤

## በእውነት እንደ አቶ መለስ ያለ መሪ የተፈጠረበት ጊዜ ነበርን?

በዚያች እያላት በደኸየች ሃገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያና ንብረትና ጥሪቱ በጥቂት ሰዎች እየተሟጠጠ በርሀብ ፣ በእርዛት በተለያዩ ሰው ሰራሽ በሽታዎች በመርገፍ ላይ ያለውን ህዝብና መብቴ ይከበር ፣የሀገሬ ዜጋና የጥቅሟ ተካፋይ ልሁን የሚሉትን ጥያቄዎች በሰላማዊ መንገድ በመግለጹ በጥይት ጭንቅላቱ እየተበተነ ያለቀውን ኢትዮጵያዊ ሣሥታውስ በእውነት እንደ አቶ መለስ ዜናዊ ያለ የሚገዛውን ህዝብ አምርሮና አክርሮ የሚጠላና የሚፈራ የሚገዛውን ሃገር መሬት ሳይጠይቁት እየለመነ ለጎረቤት ሃገራት የሚያድል በሚገዛው ህዝብ ዋይታና ሰቆቃ የሚደሰት በቀለኛ ገዥ በየትኛው ክፍለዘመን በየትኛው አህጉር ወይንም ሃገር ተከስቶ ነበር ይሆን? በማለት የቻልሁትን ታክል በሃሣብ እርቄ በአይነ ህሌናየ ስቃኝ በሙሉም ባይሆን በክፊል ማለትም በሚያስተዳድሩት ህዝብ ሰቆቃ መደሰትን ብቻ በተመለከተ ተመሳስለው ያገኘኋቸው ከቄሣር ኔሮ ጋር ብቻ ነው ቄሣሩ የወሰደው እርምጃ በፊት አስተማሪው በኋላም የፖለቲካ አማካሪው የነበረውን ሣይንቲስት፣ እሱን ሥልጣን ላይ ለማውጣት ባሏን በመዳህኒት የገደለችለትን ወላጅ እናቱንና 2 ሚስቶቹን የገደለ ሲሆን ከተማ ሲቃጠል ምን እንደሚመስል ለማየት ሲል እሮም ከተማ እንድትቃጠል አድርጎ ከተማዋ ከነንብረቷ ስትጋይና ሰው እንደሻማ ሲቀልጥ ገዥ ቦታ ላይ ከተሰራው ቤተመንግስቱ ውስጥ ሆኖ ቁልቁል በመመልከት ክራር እየመታ ይጨፍር ነበር ይለናል ታሪኩ፣

የእኛው ቄሣር አቶ መለስ ዜናዊ ይስ ምንድን ነው የሰሩት? ካልን በጥቅሉ ለመመለስ ምን ያልሰሩት አለ ፣ የክፋትና የጥፋት አይነቶችን በሙሉ አከናውነዋቸዋል፣ የስሩትን አሣዛኝ ድርጊት ለማብራራት ምንስ መግለጫ ቃላት መለኪያ መስፈርት ይገኝለታል ማለቱ የሚሻል ቢሆንም ቄሣር ኔሮን ካነሣሁ አይቀር ከእሱ ሥራ ጋር በንፅጽር ለማየት ከእውቅያኖስ ላይ በሻይ ማንኪያ የመቆንጠር ታክል ለአብነት አንድ ሁለት ማለት የግድ ስለሚል ወደዚያው ላምራ፣ አቶ መለስ ደደቢት በነበሩበት ወቅት ተገደሉ ስለሚባሉ የትግል ጓዶቻቸውና በትረመንግስቱን ከጨበጡ በኋላም ስለሞቱት ክንፈና ሀየሎም የሚወራውን ተከድኖ ይብሰል ብየ ልለፈውና ከሌሎች ድርጊቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ልጥቀስ ፣

1ኛ/ አቶ መለስ ዜናዊ ምኒልክ ቤተመንግስት በገቡ ማግሥት ቄሣር ኔሮ ከተማውን እንዳቃጠለ ሁሉ እሣቸውም አዲስ አበባ ከተማ መሃል የሚገኘውን የበቅሎቤትና ሽጎሌ የመሣሪያ ግምጃ ቤትን በማስቃጠላቸው በውስጡ የነበረው በርካታ ቦምብና የልዩ ልዩ ከባድ መሣሪያ ጥይት እየፈነዳ ከ5 እስከ 8ኪ/ሜ በመወንጨፍ በርካታ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪወችን ገድሎአል፣ አካለ ጎደሎ አድርጓል በብዙ ሚሊዩኖች የሚቆጠር ንብረት አውድሟል፣ በሺህ የሚቆጠርን ህዝብ ከቤት ንብርቱ እንዲፈናቀል አድርገዋል፣.

2ኛ/ ቄሣር መለስ ምንም እንኳን እንደ ህልማቸው ኢትዮጵያን ለማፈራረስ እንዲመች በኢትዮጵያዊነት መልክ የተተከለን ተቋም አስቀድሞ መናድ የደደቢት ቀመር መነሻ ፕሮግራማቸውና ፖለቲካዊ ግባቸው ቢሆንም ከሂውማኒቲ (ከእርህራሄ) አንጻር ቅንጣት ሃሣብ እንኳን ሣይጨምሩበት ሀገር ሲወረር ድንበር ሲደፈር ቀድሞ እየደረሰ መሷእት በመሆን የእናት ሃገሩን ልዋላዊነት በደሙ ፍሣሽ፣ በአጥንቱ ክስካሽ ሲያስከብር የኖረውን የኢትዮጵያ ሰራዊት የደርግ ስራዊት ነህ በማለት በአንድ ሥራት ፈርጀው ያለምንም መቋቋሚያና ካሣ ክፍያ በመበተናቸው ወደ ግማሽ ሚሊዩን የሚጠጋው መለዩ ለባሽ ከእነ 5 ና 6 ቤተሰቡ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ለተመጽዋችነት መዳረጋቸውና በረሃብና በእርዛት እንዲያልቅ ማድረጋቸው ብቻ ሣይሆን ለእናት ሀገሩ ህልውና መከበር በተለይም ከወራሪውና ከተስፋፊው ከሦማሌው የሲያድባሪ ጦር ጋር ሲፋለም ግማሽ አካሉን በኦጋዴን አሸዋ ቀብሮ ግማሽ አካሉን ይዞ በመመለስ በጀግኖች አምባ መጠለያ ውሥጥ ይኖር የነበረውን እጅ እግሩ የተቆረጠ አይኑ የፈረጠ ብሄራዊ ጀግና አውጥተው መስክ ላይ በመበተናቸው እንዳይራመድ፣ እግሩን፣ እንዳይጨብጥ እጁን፣ እንዳያይ አይኑን ፣ ለሀገሩ የአካል ግብር የከፈለ ኢትዮጵያዊ የትም እንደአልባሌ እቃ ተጥሎ በርሀብ እንዲያልቅ በዱር አራዊት እንዲበላ አድርገዋል አቶ መለስ፣ ከቡራትና ከቡራን አንባብያን እስኪ አስቡት!! በእውነት ሰው በገዛ ወገኑ ላይ እንዲህ መጨከን አለበት ትላላችሁ ?እኔ ግን ይህችን ጽሁፍ ስጫጭር በአጠቃላይ በወገን ላይ የደረሰውን በተለይም እነዚያን ግማሽ አካላቸውን ለኦጋዴን አባኮዳ ጥንብ አንሣ አስርክበው የተመለሱ ጀግኖችን መጨረሻ በማስታወሴ እንባየ እየፈሰሰ ነበር፣

3ኛ/ የእኛው ቄሣር አቶ መለስ ዜናዊ የቋንቋ ልዩነቱን ጌጡ አንድነቱን የክብር እሴቱ በማድረግ ተጋብቶ ተዋልዶ በፍጹም እንደ ወተትና ውሃ ተዋህዶ የኖረውን የኢትዮጵያን ህዝብ የመለያ ታቤላ በመለጠፍ አንተ እዚያኛው አንተ

እዚህኛው ናችሁ፣ ያኛው ደግሞ ከመቶ አመት በፊት የቋንቋህን ተናጋሪ በድሎ ነበርና ዛሬ የልጅ ልጅ ልጁን ተበቀለው በማለትና እንቢ ሲል ሰራዊታቸውን ልከው በብሄረሰቡ ስም ብጥብጥ እንዲነሣ በማድርግ በአጠቃላይ ከ80 በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ እርስ በእርሱ እንዲፋጅ ያደረጉ ሲሆን በተለይ በመልከአ ምድር አቀማመጡም ሆነ በዘር ግንዱ በተወሣሰበ ሁኔታ ላይ የሚገኘውንና በህዝብ ብዛቱም ከኢትዮጵያ ህዝብ ላቅ ያለውን ድርሻ የያዘውን የኦሮሞኛና የአማረኛ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያንን ነፍጠኛና ጭሰኛ በሚል ከፋፍለው ህዝብ ለህዝብ አጩፋጭፈዋል፣ መጠነሰፊ ንብረት አስደምሥሰዋል ዛሬም ቀዝቀዝ ሲል ከላይ እንዳልኩት ሰራዊታቸውን በመላክ ያነሣሱታል ፣ ምክናያቱም ሥልጣን ላይ መቆየት የሚችሉት እኛ እርስ በእርስ እስካልተስማማን ጊዜ ድረስ ነውና እዚህ ላይ ኔሮና አቶ መለስ ዜናዊን ስናወዳድር የእኛው ነፍስ ገዳይነት ልቆ ይታያል ፣ ኔሮ ለስልጣኑ ሲል ያስገደለው ከእሱ በፊት የነበረውን ንጉሥ ብቻ ነው፣ አቶ መለስ ግን እስካሁን ያለቀው ቢደመር በአስር ሺወች የሚቆጠር ሣይሆን አይቀርም፣

4ኛ/ ምርጫ 97ን ተከትሎ የደረሰውን እልቂት ዓለም የሚያውቀው ነውና አልገባበትም ግን ግን አቶ መለስን ከኔሮ ጋር የሚያመሳሥላቸውን አንድ ነጥብ ለመጥቀሥ ያህል ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ/ም የአቶ መለስ ቅልብ የአጋዚ ሰራዊት ህፃን ፣አሮጊት፣ ሽማግሌ፣ ወጣት ሣይመርጥ በእየቤቱ እየገባ ሲያርድ መንገድ ላይ ያገኘውን ሁሉ በስናይፐር ጥይት ጭንቅላቱን በመበተን ጥሎ ሆስፒታል በመውሰድ ቤተሰብ አስከሬን ሲጠይቅ ገንዘብ እንዲከፍል ሲያስገድድ አዲስ አበባ ከተማ የደም አውድማ ሆና ለቅሦ ፣ዑዑታ ነግሦ በአጠቃላይ አየሩ የጭንቀት የሀዘን ድባብ አርግዞ ህዝብ በደም እምባ እየተራጨ በአለበት ወቅት አቶ መለስ ዜናዊ በሽህ መሃመድ አላሙህዲን ደጋሽነት የልጃቸውን ልደት በሸራተን ሆቴል በማክበር ይዝናኑ ነበር፣ ኔሮ ከተማ አቃጥሎ እሱ ገኘ ቦታ ላይ ከተሰራው ቤተመንግስቱ ቁጭ ብሎ እየተመለከተ ክራር በመምታት ይዝናና እንደነበረ ሁሉ፣ እንግዴህ ሁለቱን ከሚያመሣሥሏቸው ብዙ ነገሮች መካለል ለአብነት ጥቂቶቹን ጠቃቀስሁ እንጅ የአቶ መለስ ዜናዊን የጭካኔ ተግባር በሙሉ ዘረዘርሁ ማለት አይደለም፣ የእሣቸውንም ድርጊት የመዘከሩ ድርሻ የታሪክ ምሁራን ስራ ነው ብየ ባምንም በበኩሌም ቢሆን በቃል ያለ ይረሣል በጽሁፍ ያለ ይወረሣል እንደሚባለው ነውና እግዚአብሔር ከፈቀደ በመጽሀፍ መልክ አዘጋጅቸ ለታሪክና ለትውልድ ለማስተላለፍ እሞክራለሁ፣

እንግዴህ ከላይ በጠቃቀስኳቸው ነጥቦች ምክንያት በእኔ እይታ እብደት በሚመስል አስተሣሥባቸውና ነገን የሚያዩበት የጠበበ አይነህሌናቸው ለአቶ መለስ ዜናዊ ተወዳዳሪ ያገኙሁላቸው ቄሣር ኔሮን ነው ፣ መቸም ውሎ ውሎ ወደቤት፣ ኑሮ ኑሮ ወደ መሬት አይቀሬ ናቸውና ቄሣር ኔሮን መላከሞት መጥቶ ሲያጣድፈው ዛሬ ዓለም ታላቅ አርቲስት አጣች አለ ይባላል ፣ የእኛውስ ምን ይሉ ይሆን? ነው ሞትንም እንደ ኢትዩጵያ ህዝብ እሸውደዋለሁ ወይንም በኢጋዚ ሰራዊት በጥይት ጭንቅላቱን አስበትነዋለሁ ብለው እየተዘጋጁ ይሆን? መጨረሻቸው ያጓጓኛል፣

## ኢንቨስተር ማለት ምን ማለት ነው?

ነገርን ነገር ያስከትለዋል እንደሚባለው ሁሉ ስለ አቶ መለስ ዜናዊ የጭካኔ ስራ ሳብራራ አንድ ቦታ ላይ ሼህ መሃመድ አላ ሙህዲንን አንሥቸ ነበርና ከሰሞኑ ስማቸው ተደጋግሞ በመገናኛ አውታሮች ሲነሱ ከመስማቴ ጋር ተዳምረው በዚህ ጽሁፍ አንድ ነገር እንድል ገፍተውኛል፣ ብዙም ባይሆን እንደሰማሁት በአንድ በኩል ያለው ከሃገራችን ፖለቲካ ጋር በማያያዝ ተቃውሞውን ሲሰነዝር ሌለኛው ደግሞ ያለሙትን አንድ ሁለት እያለ በመጥቀስ ሲያሞግስ አዳምጫለሁ፣ በበኩሌ ተቃዋሚውን አልፈ ደጋፊውን በሁለት መንግድ ነው የማየው፣ አንደኛው ወያኔዎች ስለሚሆኑ መቸም ለጥፋት የቆሙ ናቸውና አጥፊን መደገፋቸው ስለማያሥገርም ብቻም ሣይሆን ካድሬዎቻቸውም ስለሆኑ ችግር የለውም፣ ሁለተኛው ግምቴና ያሣሰበኝ ግን ምናልባት ውስጡን ሣያውቅ ላይላዩን እያየ ብቻ መደገፉን የታደመ ሰው ካለ ነው፣ ምክናየቱም ድሮ እኔም ውስጠሚስጥሩ ሣይገባኝ በብዕር ሥም ለነፃው ፕሬስ ሣቀርባቸው በነበሩ አርቲክሎች ሸሁን ሣደንቅ ስለነበር ነው ፣ በዚያኔ የጻፍሁትን ዛሬ ሣነብበው ለእራሴ አፍራለሁ፣ እንዲያውም በዚሁ እርዕስ ማለትም ኢትዩጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች በሚለው ዜጋ መጽሄት 2ኛ አመት ቁጥር 8 ሚያዚያ 1993 ዓ/ም እትም ይዞት በወጣው ጽሁፈ ላይ ለኢትዩጵያ መሪነትም ተመኝቻቸው ነበርና ዛሬም ሚስጥሩ ያልተገለጸለት የዚያኔው የእኔ አይነት ሰው ሊኖር ስለሚችል ስለሸሁ ዘግይቶ ቢሆንም የገባኝንና የማውቀውን ለወገኖቼ ማካፈሉ ጠቃሚ ስለመሰለኝ ነው የገባሁበት፣ እናም በመጀመሪያ ደረጃ ኢንቨስተር ማለት ምን ማለት ነው? ሸሁስ ኢንቨስተር ናቸውን? የሚለውን ጥያቄ መልስ መስጠት ተገቢ ይመስለኛል፣ እኔን እንደሚገባኝ ኢንቨስተር ማለት የእራሱን መዋለ ነዋይ በአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ልማት ላይ የሚያፈሥ ማለት

ነው፤ አይ የአንድን ሃገር ንብረት የሚዘርፍ ነው ኢንቨስትር የሚባለው የሚል ስለማይኖር በዚህ ሁላችንም እንስማማለን ብየ አስባለሁ፤ የሚቀጥለው ሸህ መሀመድ አላ ሙህዲን በኢትዩጵያ ኢንቨስተር ናቸውን? የሚለው ጥያቄ ነው በበኩሌ ምክናያታዊ ሆኜ ለዚህ ጥያቄ የምሰጠው መልስ በአጭሩ ሸሁ በኢትዩጵያ ኢንቨስተር አይደሉም ነው፤ ምክናያቴም ሰውየው ወደ ኢትዩጵያ ሲገቡ ይዘውት የመጡት ነገር ቢኖር የቢዝነስ ዘዴአቸውን ብቻ እንጅ በገንዝብም ይሁን በአይነት ያስገቡት ምንም ነገር ሥለሌለ፤ አንኳሩ ጥያቄ ታዲያ ይህ ሁሉ ሃብት ከየት መጣ? የሚለው ይሆናል ብየ አስባለሁና መነጋገር ያለብንም በዚህ ላይ ይመስለኛል፤ በሙሉ መዘርዘር ጊዜን ከማባከን አንፃር ባይቻልም ለአብነት ያህል አንድ ሁለት ልበል፤

1ኛ/ ሸህ መሀመድ አላ ሙህዲን ኢትዩጵያን አለማለሁ ብለው ሲገቡ የመጀመሪያ ስራ ያደረጉት የአልታድ ኮንስትራክሽንንና የሸራተን ሆቴልን ፈቃድ ማውጣት ነው ፤ ምክናያቱም በወቅቱ የግንባታ ቁሣቁሦች እጥረት በኢትዩጵያ ስለነበር እነዚህ 2 ፈቃዶች የሚይያስገኙትን ትርፍ በማስላት ነበር በቢዝነስ ዘዴያቸው መሰረት ፈቃዶቹን ይዘው ወደ ኢትዩጵያ ንግድ ባንክ በመሄድ የውጭ ንግድ ሂሣብ (ዔ ልሲ)በመክፈት ከኪሳቸው አንድ ሣንቲምም ሣያወጡ በባንኩ ገንዘብ የግንባታ ቁሣቁሦችን በገፍ በማስገባት ከገቢግብር (ከቀርጥ) ነፃ ከጉምሩክ በማውጣት ለሃገር ውስጥ አካፋፋይ ነጋዴዋች በጅምላ ማስረከቡን ቀጠሉበት የመጀመሪያው ትርፍ መዛቅ የጀመረው እንግዴህ ሃገሪቷ ማግኘት ከሚገባት የገቢ ግብር ላይ ነው፤ በውቅቱ ጉምሩክ ይሰራ የነበረና ዛሬም ሸሁን በሚመለከት ማስረጃዎቹን ይዞ ቀን እስከሚወጣ ከሚጠባበቅ አንድ ወዳጅ ጋር ሸራተን የተመረቀ ዕለት በአጋጣሚ ተገናኝተን አንድ አካባቢ ነበር የተቀመጥነውና ሸሁ ንግግር ሲያደርጉ ይኸው እኛ 8መቶ ሚሊዩን ዶላር አውጥተን ሰርተናል፤ ከእንግዴህ መዝናናቱ ለኢትዩጵያ ህዝብ ፋንታ ነው ብለው ነበርና፤ ያ ጉምሩክ ይሰራ የነበረ ወዳጀ ከእኛ በማያልፍ ድምጽ የንዴት ሣቅ እየሣቀ በገንዘብህ ሰራህልን እንዲህም አድርጎ ስራ የለ ስለአለ ከንክኖኝ ምን ማለቱ እንደሆነ ስጠይቅው ከሚያስገባው የግንባታ ዕቃውች ላይ ከገቢ ግብር(ቀርጥ) ሃገሪቷ ታገኘው ከነበረው አንድ አራተኛው አይሆንም እዚህ ሆቴል ግንባታ ላይ የዋለው ነበር ያለኝ፤ ተመልከቱ እንግዴህ ውድ አንባብያን ሸራተን የተራበት 8መቶ ሚሊዩን ዶላር ብቻ ሣይሆን ከሃገሪቱ ገቢ ላይ የተዘረፈው ሌላ 3 እጥፍ ከሃገር ኮብልሏል ማለት ነው እና ይህ ነው የሸሁ ኢንቨስተርነት በኢትዮጵያ፤

2ኛ/ በመንግስት ይዞታ ሥር የነበሩ የልማት ተቋማትን ወደግሉ ሴክተር ማዛዋር በሚል ሥም ታላላቅ ፋብሪካዋችን እርሻዋችን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ወ.ዘ.ተ. ለሸሁ ያለጫረታ በሽያጭ ሥም በነፃ የተሰጣቸውን በሙሉ መዘርዘር አንባብያንን ማሰልቸት እንዳይሆንብኝ፣ ስለሰጋሁ ለአብነት 3ቱን ብቻ ልጥቀስ

2.1 ፔፕሲ የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ በየከተማው እስካለው ቅርንጫፉ አላወጣም ቢባል ከ5 እስከ 6 መቶ ሚሊየን ብር ማውጣት ሲችል ለሸሁ በ 50 ሚሊዎን ብር ብቻ ነው የተሰጣቸው ፣ ክፍያውንም እሣቸው ከኪሣቸው 10ብርም ሳያወጡ ሰርተው ይክፍሉታል በሚል ሽፋን ባንክ ነው የፈጽመው፣

2.2 በጎንደር ጎጃም እርሻልማት ሥር ይተዳደሩ የነበሩ ላይ ብር ፣ ታች ብር፣ አዮና ኡመራ እርሻ ልማቶች በርካሽ ተሸጡ ቢባል ከአንድ ቢሊዩን ብር ያላነሰ ማውጣት ሲገባቸው ለሸሁ በ43 ሚሊዩን ብር ነው የተሰጣቸው ክፍያውንም ያው እንደ ፔፕሲው ባንክ ነው የፈጸመው፣

2.3 በአማራው ክልል ቡሬ ከተማ ላይ የተተከለውን የቡሬ ባጉና ማዕድን ውሃና ለስላሣ መጠጦች ፋብሪካን አንድ መቶ ሚሊዩን ብር ባለሃብቶች አዋጥተው አንድ መቶ ሚሊዩዎን ብር ክባንክ ተበድረው በተከሉት አንድ አመት ሣይሰራ ከእነሱ ተነጥቆ ቢያንስ መነሻው የባንኩ እዳ መሆን ሲገባው ሁለት መቶ ሚሊዩን ብር የተገዛ ፋብሪካ ለሸሁ በ27ሚሊዩን ብር ነው የተሰጣቸው ክፍያውም የተከናወነው እንደ ሌሎቹ በባንኩ በኩል ነው፣

እንግዴህ ውድ አንባብያን በዚህ አይነት ነው ሸህ መሀመድ ከ30 በላይ የሃገር ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆኑ አትራፊ የልማት ተቋማትን በነፃ በመውሰድ የሚያስገኙትንም ገቢ በሙሉ ወደ ውጭ ሃገር በማጀርግ ላይ የሚገኙት፣

እዚህ ላይ የወርቁንና የእብነ በረዱን ጉዳይ ያላነሣሁት ኢትዮጵያ በእነዚህ 2 ብርቅየ ማዕድናት የደረሰባትን ኪሣራ የማያውቅ አንባቢ አይኖርም ከሚል ግምት ነው፣ እናም ስለቃሉ አንባብያንን በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅሁ ሸህ መሃመድ አላ ሙህዲን ኢንቨስተር ሣይሆኑ በኢትዮጵያ ህዝብ ደም ያበጡ ዘራፊና ተራ የፖለቲካ ደላላ ናቸው፣ ነገሩ ሣይገባችሁ ሰውየውን የምታደንቁ ካላችሁ እውነቱ ይኸው ነው፣ በአጠቃላይ ግን ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ የወያኔ ካድሬነት የማይፈልጉ ሰወችን (ባለሀብቶችን) ማጥመጃ ሲሆን ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ደግሞ የኢህአዴግ መሰረታዊ ድርጅት ጽ/ቤቶች ናቸው የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 15/84 ስለሚያማልል አንድ ኢንቨስተር እውነት

መስሎት አለማለሁ ብሎ ሲገባ በመጀመሪያ ላይ በሩ ወለል ብሎ ይከፈትለታል፣ ቆየት ብሎ ያለውን ጥሬት ማፍሰሱ ሲረጋገጥ በቀጥታም ይሁን በተዛዋሪ ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በአንዱ የአባልነት ሰነድ እንዲሞላ ይጠየቃል፣ ፈቃደኛ ከሆነ በደህና ይቀጥላል እንቢ ካለ ግን በመንገዱ ሁሉ እንቅፋት ይደረደርለታል፣ አይደለም በነፃነት ማልማት መሬትን መርገጥ፣ አየርን መተንፈስ ሁሉ ወንጀል ይሆኑበታል፣ ከዚያ በኋላ ከሣሹም ዳኛውም አቃቤህጉም ምስክሩም እራሱ ወያኔ ስለሆነ የውሸት ወንጀል ተፈብርኮ ውሎው ፍትህ አልባው ፍርድ ቤት አዳሩ እስር ቤት ይሆናል፣ በእኔ የደረሰ ይኸው ነው፣ ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ እንደሚባለው ነውና ሌሎች ወገኖቸ በወያኔ ወረቀት ላይ የሰፈረ የቃላት ጋጋታ ውስጡ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ መሆኑን ትረዱት ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ጠቁሜ ማለፉን ወድጀዋለሁ፣

## ከመጨረሻው መጨርሻ ጠርዝ ላይ የቆምን ይመስለኛል፣

ይህንን አባባል ለማስረገጥ በማስረጃ የተደገፈ ትንታኔ መስጠት የሚያስፈልግ አይመስለኝም ፣ ምክንያቱም ሃገራችን ያለችበትን ሁኔታ አንዳችን ለአንዳችን ነጋሪ ሆነን በምንቀርብበት ጊዜ ላይ አይደለምና ያለነው እኔ ማለት የምፈልገው፣ አንድ ነገር ቢኖር ግን ወደድንም ጠላንም በአጭር ጊዜ መድረሣቸው የማይቀር 2 አማራጮች ይጠብቁናል፣ እነሱም እርስ በርስ መጎሻሸሙን ትተን ለአንድነት በአንድነት በመቆም ሃገራችንን ከጥፋት እራሣችንንም ከታሪክና ከትውልድ ተጠያቂነት ማዳን ወይንም በያዝነው የእርስ በርስ ንትርክ ጊዜያችንንና ሃይላችንን ስናባክን ሃገራችን ጠፍታ እኛም ሞታችንን ቆመን የምናስተናግድ ሀዘንተኞች መሆን የሚሉት ናቸው ፣ እንግዴህ በበኩሌ ከወያኔ በቀር የኢትዩጵያንና ኢትዩጵያዊነትን መጥፋት የሚፈልግ ይኖራል ብየ መገመት ይከብደኛል፣ ታዲያ ሃገርና ወገናችንን ከወደድን እንዳይጠፉም ከፈለግን የነገር ድህን እያከበርን ጥቃቅን ልዩነቶችን እያሣደግን ከመናቆር ይልቅ ልትጠፋ ለተቃረበችዋ ሀገራችን ስንል የማንተውበት ምክናያቱ ምንድን ነው? አባቶቻችን፣ አያቶቻችን፣ ቅድመአያቶቻችን ወ.ዘ.ተ. በኢትዩጵያ ላይ ከ13 ጊዜ በላይ የተሰነዘረባትን ወረራ መክተው የመለሱት በደም እንኳን የሚፈላለጉ ቢሆን ሃገር አጥፊ ሲመጣ ቂማቸውን እንደ ውሃ ይፍሰሥ እንደጋኛ ይንፈስ በማለት ትተው የሃገርን ጉዳይ በማስቀደም በጋራ በመሰለፍ እኮነበር፣ በእውነት እኛን የነካን ምን ይሆን? በሌለች ሃገር ላይ መባላት ኢትዩጵያ የምትባል ሃገር እኮ በነበር ልትተካ ምንም እየቀራት አይደለም ፣በእኛ አለመስማማት በእኛ ድክመት የወያኔን ዕድሜ

ካራዘምነው የቤት ስራውን ማጠናቀቂያው ከሆነው የመጨረሻ እርከን ላይ ነው ያለው፣ እረ ጎበዝ ምን ነካን ይሆን?!!! አትሳቁብኝና አሁን አሁን ወያኔ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠር ይቀለዱ ከነበሩ በጣም ብዙ ቀልዶች መካከል አንዱን ከቀልድነት የዘለለ እውነት ይሆን ወደማለቱ እየዳዳኝ ነው፣ አንባብያንም ከእውነታው አለምና ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ በአንድ ቃል እየሆነው ካለነው ጋር በማገናዘብ ታዩት ዘንድ የዚያኔውን ቀልድ ልንገራችሁ፣ ምንድን ነበር ቀልዱ መስላችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የምንታዘዘውን ሁሉ እሺ እንድንል፣ የተጫነብንን ሁሉ እንድንሸከም፣ በግመልና በአህያ በብሔራዊ ጉዳያችንና በጋራ ችግራችን ላይ ተቀራርበን እንዳንወያይ፣ እንዳንስማማ፣ እርስ በርስ እንድንናከስ በውሻና በድመት ፈሪዎች ፣ሆዳሞች፣ተጠራጣሪዎች እንድንሆንና እንዳንተማመን በጅብ በሱዳን ባለሙያዎች መተት እየተሰራብን ነው፣ እየተባለ ይቀለድ ነበር፣ አሁን ይህ ሁሉ እየተፈጸመ አይደለምን?

ውድ አንባብያን አሁን ትልቁ ጠላት ከፊታችን ተገትሮ እርስ በርሣችን የምንቧጨቅበትን የሚመረምር ዳኛ ቢገኝ ለጭብጥ የሚበቃ በማስረጃ የተደገፈ በደል የደረሰበት ሰው አይገኝም በአንድነት ሀይሉ መካከል ማለቴ ነው ፣የተበደለ ቢኖር እንኳን ከላይ እንዳልኩት ከእዚያ የከፋ ነገር ስለአለ ለሀገር ጉዳይ ቅድሚያውን መስጠት ተገቢ ነውና እባካችሁ ወገኞቼ እስኪ ሁላችንም ቆም ብለን አንድ ገዜ እንደገና እናስብበት፣ እስኪ እራሣችንን እልህ ከሚሉት በሽታ እንፈውሰው ፣እስካሁን አየነው እኮ ከጥፋት በቀር የሰጠን ጥቅም የለም አሻግረን እንይ እስኪ፣ ጎበዝ ሀገርን የምታክል መተኪያ የማይገኝላት ታላቅ ንብረት ባለሃገር እነትን የሚያክል መተኪያ የማይገኝለት ታላቅ ክብርና ኩራት ልናጣ፣ ልንዘረፍ ፣ ልንገፈፍ፣ እርታናችንን ልንቆምና ነገም ልጆቻችንን ሃገር አልባ ጅሆተኛ ልናደርጋቸው ያለነው ከመጨረሻው መጨረሻ ጠርዝ ላይ ነው፣

እናም ከአብራኳ ባወጣችው ልጅ አካሏን አጥታ እያላት ተርባ፣ተጠምታ በወላድ መካንነቷ እያዘነች፣ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ብቻ ሣይሆን ወደ ልጆቿም በመዘርጋት የድረሱልኝ ጥሪዋን በማሰማት እየተማጸነች ለአለችው ለእናት ሀገራችን ኢትዮጵያ መልሣችን አንድነታችን በጋራ መቆማችን ሊሆን ይገባልና ይህንን ነገር ምኞት ሣይሆን ውሣኔ ፣ ፍላጎት ሣይሆን ግዴታ፣ ለንማድርግ ህሌናችንን እናዘጋጅ እባካችሁ በግልም ይሁን በድርጅት ልዩነታችንን አቻችለን ቢሆን በጋራ እንታገል ካልሆነም ወያኔ በሚሰጠን የቤት ስራ በመጠመድ እርስ በእርስ መቧጨቃችንንና የተቃዋሚ ተቃዋሚ ሆነን

መሰለፋችንን ማቆሚያ እናብጅለት እያልሁ በምትከተለዋ የግጥም ስንኝ ቋጠሮ ልሰናበት.፤

እኔስ ሰው ናፈቀኝ ኢትዮጵያዊ ጀግና፣
ህዝቡን የሚያከብር በአንድነት የፅና፣
   እስኪ ቀስቅሷቸው ጀግኖች ይናገሩ፣
   የአገር ፍቅር ማለት ምንነበር ሚስጥሩ፣
እስኪ ጠይቁልኝ ይናገር መቅደላ ፣
የአንድነቱን ዋልታ እንዴት እንደበላ፣
      ይናገር ያምድር ቅጠል ይሁን እሣር፣
      ካሣ የተሰዋው ለምን እንደነበር፣
ነበር ወይ ፈልጎ የግሉን ድሎት፣
ወይስ አምሮት ይሆን ፈልጎ መሞት፣
የአውደ ውጊያው መልካ ሚስጥሩን ያውሩት፣
     ምንም ዛሬ ሱዳን ቆርሶ ቢውስዳት፣
     ልጓዝ ወደቋራ ወደካሳ ቤት ፣
ኡመራ መተማ የቃል ኪዳን ቦታ፣
በእምነት የተቋጨው በክህድት ተፈታ፣
ይነገር ለቴዲ ዩሐንስም ይስማ ፣
ለሱዳን መሸጡን ኡመራ መተማ፣
የነፃነት ቀንዲል የአንድነት ምሰሦ፣
ይጠራ ምኒልክ ይምጣ ተመልሦ፣
ያቆያትን ሀገር አኩርቶ አስከብሮ ፣
ዩሐንስ ለደርቡሽ አንገቱን ገብሮ፣
ዛሬ መለስ ሸጣት በብር ተደራድሮ፣
ጀንበር ዘቀዘቀች ሙብቱን ለተቀማ ፣
ይብቃ ቀን መጠብቅ ከእንግዴህ ወዲያማ፣
እነሱም ገፉፉን እኛም ሄድን አፋፍ ፣
ሊታይ ነው ጉዱ ማን ቀድሞ እንደሚያልፍ፣
ጀግና ልበሙሉ የእንቢታ ገበሬ፣
እንደዚያ እንደጥንቱ ይገኛል ወይ ዛሬ፣
የዘር የሃይማኖት መርዙ ያልበከለው፣
ያምቻ ጋብቻ ጥቅም ያላወረው፣
ምርጥ የኢትዮጵያ ልጅ እሱ ጀግና ማንነው፣
ሐገሬ ኢትዮጵያ ብሎ ሚመሰክር
መሆኗን ያመነ አንድ ሃገር አንድ ምድር፣
ማግኘት የግድ ሆኗል ሳይውልም ሣያድር፣

የእናት ሀገር ፍቅር ምን እንደነበረ፣
እንደአርያ ነትም ህዝብን ያስተማረ፣
ጣይቱን የሚያክል ጀግናም ሴት ነበረ፣
ከሞት እንደሁ ላልቀር የትም ተደብቄ ፣
ለምን እንዲህ በረርሁ ከሃገሬ እርቄ፣
እምየ እናታለም ኢትዮጵያ ሀገሬ፣
ከአንች ተወልጀ በአንች ሣምር ኖሬ፣
በአንች ላይ አርሼ ነግጀ ከብሬ፣
በችግርሽ ጊዜ ተጓዝሁ ፊቴን ዙሬ
እንቢ!! እመለሣለሁ በለመደው እግሬ
ዛሬም ካንች ይሁን ሞትና መቃብሬ፣
ዛሬም ካንች ይሁን ሞትና መቃብሬ

ማተቤ መለሰ ተሰማ
ሐምሌ 2000 ዓ/ም

የኢሜል አድራሻ: matebemelese@yahoo.com

ከግጥሞቹ ውስጥ አንዳንዶቹን ከተለያዩ ጽሁፎች ላይ የወሰድኳቸው ሲሆን ብዙቹ የእራሴ ናቸው፥